# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
## *Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*

## የሕዝብን መብት በጠመንጃ ማፈን ጥፋትን እንጂ ሰላምን አያመጣም

ከኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ የተሰጠ መግለጫ

ከሁሉ አስቀድመን በአማራ ክልል ውስጥ በሚደረገው ሕዝባዊ ትግል ሕይወታቸውን ላጡ ኢትዮጵያውያን ሁሉ የተሰማን ጥልቅ ሐዘን ለመግለጽ እንወዳለን፣ ለቤተሰቦቻቸውም መፅናናቱን እንመኛለን፡፡

ብሔር፣ ብሔረሰብ የሚለው ዕንሰ-ሃሳብ በተወሰነ የሰው ልጅ የኤኮኖሚና የማኅበራዊ ዕድገት ደረጃ የሚፈጠር፣ በሂደትም በኤኮኖሚና ማኅበራዊ ዕድገት እየቀጨጨ ሄዶ የሚጠፋ ተሸጋጋሪ ማኅበራዊ ሥሪት ነው፡፡. ብሔር፣ ብሔረሰብነት የባህሪ፣ የባህልና የቋንቋ መገለጫ መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ እነዚህን ሥሪቶች መሠረት አድርጎ ግን በኤኮኖሚ የዳበረ፣ በዴሞክራሲ የታነፀ፣ ሕግንና ፍትኅን ያማከለ፣ የፀና ሃገር መገንባት አይቻልም፡፡ ከዜግነት የሚጣረሰውን ትምክህተኝነትን፣ ጠባብነትን፣ ዕብሪትን መሠረት አድርጎ ጠንካራና ሕዝባዊ ሃገርን ለመገንባት ማሰብ፣ ሃገር በድቡሽት ላይ እንደተሠራ ቤት ትሆንና ማንኛውንም ፈተና ለመቋቋም ፅናቱ አይኖራትም፤ አሁን እንደሚታየው ምንጊዜም የፍርሻ፣ የሁከትና የዋይታ ቤት ከመሆን አትድንም፡፡

የኤኮኖሚያዊና ታሪካዊ የሰው ልጆች ዕድግት የሚያሳየን ሃቅ ይህ ሆኖ፣ በዘመኑ የጎለበተው ህወሓት ሕዝብን በቋንቋና በወሰን ገደቦ፣ ዘውግን ያማከለ የፅንፈኛ ብሔርተኞች ሥሪት አዋቀረ፡፡ ፌደራላዊ አገዛዝ ብሎ ራሱ ብቻ በበላይነት የሚያዝበት ፍጹም የተማከለ አሃዳዊና ጨፍላቂ መንግሥት አቋቋመ፡፡ ይባስ ብሎ በዕብሪተኛ ገዥዎች ዝንተዓለም ሲገፋ፣ ሲጨቆን፣ ሲታሰር፣ ሲፈነገል የኖረውን የአማራን ሕዝብ፣ የሌሎች ኢትዮጵያውያን የመከራ ምንጭ፣ የጭቆናቸው መሠረት፣ የጉስቁልናቸው መነሻ ተደርጎ ተፈረጀ፡፡ የህወሓት

መንግሥትና አጋሮቹ አማራን ከኢትዮጵያውያን ወገኖቹ ሊነጥሉት፤ ሊያናችፉት፣ ደም ሊያቃቡትና በቀል ሊያወርሱት ለበርካታ ዓመታት ያላሰለሰ ተንኮል ሸረቡበት፡፡

"ከጅብ ጅማት የተሠራ ክራር ቅኝቱ ምንጊዜም ልብላው ልብላው ነው" እንዲሉ ህወሓትን የተካው የብልጽግና መንግሥትም ኢህአዴጋዊ ባሕሪውን ቀጥሎ በአማራው ላይ ዘመቻውን የጀመረው ገና ከጠዋቱ ነበር፡፡ በብልጽግና መንግሥት አገዛዝ አማራው በማንነቱ ከቀየው ተፈናቅሏል፤ በግፍ ታርዷል፤ ጥሪቱን ተወርሷል፡፡ ይህ ሁሉ መከራ በአማራው ላይ ሳያባራ እየወረደበት እንኳን ሃገርን አፈርሳልሁ ብሎ በዕብሪትና በትዕቢት ህወሓት ሃገር ሲወር አማራው ሞፈሩን ሰቅሎ፣ ጠመንጃውን ወልውሎ፣ በጀግንነት፣ በፋኖነት ተዋጋ፣ ተዋደቀ፣ ሃብቱን ጥሪቱን ገበረ፡፡ ጦርነቱ ሲጠናቀቅል ደግሞ ነፍጡን ከቆጥ ሰቅሎ ሞፈሩን አነሳ፡፡ ቢሆንም የብልጽግና መንግሥት የአማራውን ተጋድሎ ከመጤፍ ሳይቆጥር በአማራው ላይ የግፍ ዘመቻውን ቀጠለ፡፡ አማራውን ማፈናቀልን፣ መግደልን፣ በጅምላ ማሠረን ተያያዘው፡፡ አያት ቅድመ አያቶቹ ከሌሎች ወገኖቹ ጋር መሥርተው እዚህ ባደረሷት የአገራችን ዋና ከተማ አዲስ አበባ እንዳይገባ ተከለከለ፡፡ ህወሓት ካደረሰበት መከራና ውድመት ሳያገግም፣ ነገር የግሪንቢጥ ሆነና አገሩን ወረቱን ፈጅቶ፣ ጠገሬታውን መትሮ፣ ልጁን አጥቶ፣ ሰብዕናውን ተነጥቆ የሰው ምስሉ ብቻ በቀረበት፣ ሕገ-መንግሥቱ ተጥሶ በአማራው ሕዝብ ላይ ወታደር ተመራበት፡፡ "መበደል ወታደር በድሏል፤ ግን ባላገር ይካስ" ተባለና፣ አማራ ወንጀለኛ፣ ቀማኛ፣ ጃውሳ፣ ምንትስ ተብሎ ተፈረጀ፡፡ የጦር አሸኬላ ዙሪያውን ተጠምዶበት፣ የነፍጥ ጨንገር እያፏጨበት እንደገና ተዋርዶና ተንቆ ለብልጽግና መንግሥት ተመቻችቶ እንዲዋቀር በኃይል ሊያንበረክኩት ዘመቱበት፡፡ እንግዲህ ለዘመናት ሳያሰልስ በአማራው ላይ የተፈጸመውን በደሉን፣ ብሶቱን ደጋግሞ ቢያሰማም ጀሮ ዳባ ልበስ መባሉ ነው የአማራውን እምቢተኝነት የፈጠረው፡፡ በቃኝ ብሎ ነፍጥ አንስቶ ለህልውናው እንዲታገል የተገደደው፣ ፋኖነቱን እንደገና ያዋለደው፡፡

ዛሬ የአረር ጢስ እንደ ጉም ሸፍኖት፤ ታንክና መድፍ ጋርዶት፤ የሀገር አንድነት ብዥ ብሎ በሚታይበት፤ ሀገር የሚለው ፅንሰ-ሃሳብ እየተስለመለመ በሄደበት፤ የሀገሪቱ ኤኮኖሚ ሥጋና ደሙን ጨርሶ በአፅሙ እየተውተረተረ ባለበት ሁኔታ፣ የሀገርን ህልውና ለማስጠብቅ መንግሥታዊ ጥንቃቄ፣ ብልህነትንና ልበ-ሰፊነትን ይጠይቃል፡፡ እንደ እሳተ ጎመራ የፈነዳን

የሕዝብ ቁጣ፣ ዕብሪትን፣ ገንዘብን፣ ጠመንጃን ምሰሶ አድርጎ ለመፍታት መሞከር ፍጹም ሃላፊነት የጎደለው ኢ-ሕዝባዊ ድርጊት ነው፡፡ አማራን በማንነቱ በጅምላ ማሠር፣ ማሳደድ፣ እራሱ የብልጽግና መንግሥት እመራበታለሁ የሚለው ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 14፣ “ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ፣ በሕይወት የመኖር፣ የአካልና ደኅንነት መብት አለው” የሚለውን ጥሶ የዜጎችን መብት ማፈን፤ የመከሰስ መብታቸው በሕግ የተከበረ መሆኑ እየታወቀ የፓርላማ አባላትን ከቤታቸው ወስዶ ማሠር፣ ሕገ=መንግሥታዊ ጥሰት ከመሆኑ በላይ ችግሩን ያባብሰዋል እንጂ መፍትሄ አያመጣም፡፡ ኢሕአፓ የችግሩን ውስብስብነትና በአግባቡ ባይፈታ በሀገር ህልውና ላይ ሊያመጣ የሚችለውን አደጋ በማገናዘብ መንግሥት የሚከተሉቱን እርምጃዎች ያለመንም ቅድመ ሁኔታዎች ተግባራዊ እንዲያደርግ አጥብቆ ይጠይቃል፡፡

1. የመከላከያ ሠራዊትን ከአማራ ክልል በአስቸኳይ ማስወጣት፣
2. ጊዜያዊ አዋጁን መሰረዝ፣
3. በአዲስ አበባና በመላው ኢትዮጵያ በማንነታቸውና በፖለቲካ እምነታቸው የታሠሩ ዜጎችን በአስቸኳይ መፍታት፣
4. በአማራ ሕዝብ ላይ ለዘመናት የተፈጸሙት የፖለቲካ፣ የኤኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የሥነልቦናዊ ጭቆናዎች በዓለምአቀፋዊና ሃገራዊ ነፃ ተቋማት ተጠንተው ተገቢው ፍትኅ እንዲሰጥ ማድረግ፣
5. በአማራ ክልል በብልጽግና አስተዳደር ላይ ሕዝባዊ ውሳኔ ማስደረግ፣ ለሌሎች ክልሎችም ተመሳሳይ ዕድል መስጠት፣
6. የአማራ ሕዝብ ያነሳቸው የኅልውና ጥያቄዎች፣ ደህንነቱና ሙሉ መብቱ እስኪረጋገጡ ድረስ ትጥቅ የማስፈታትን ጉዳይ በይደር ማቆየት፣
7. የወልቃይት፣ የጠለምት፣ የጠገዴ፣ የራያ አስተዳደሮች አሁን ባሉበት እንዲቆዩ ማድረግና ሁኔታው ሲፈቅድ በውይይት እንዲፈቱ ማድረግ፣
8. ለተፈናቀሉ ወገኖች ሀገራዊና ዓለማቀፋዊ ያልተገደበ ዕርዳታ እንዲደረግ፣ የመልሶ ማቋቋም ተግባር ውሎ ሳያድር በአስቸኳይ መጀመር፣

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ኢ. ሕ. አ. ፓ
THE ETHIOPIAN PEOPLES REVOLUTIONARY PARTY
EPRP

9. በመላ ሃገሪቱ ውስጥ የሚደረጉ ማናቸውም የማሠር፣ የመግደል፣ የማፈናቀል እርምጃዎች በአስቸኳይ እንዲቆሙ ማድረግ፣

10. የተገደቡ የዴሞክራሲ መብቶች ያለምንም ቅድመ ሁኔታዎች መልቀቅ፣ ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ የሚከናወኑ እሥራት፣ አፈሳና አፈና በአስቸኳይ ማቆም፣

11. በመገናኛ ብዙሃን ላይ የሚደረገው አፈናና በጋዜጠኞች ላይ የሚደረገው እሥራት በአስቸኳይ ማቆም፣

12. የጎሳ ፖለቲካ በሕግ እንዲታገድ አጥብቀን እንጠይቃለን፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!!

ህወሓት/ወያኔ ገና እንደ ድርጅት ሲቋቋም ጀምሮ ሲያራምደው የነበረው አክራሪ የብሔርተኝነት አቋሙን፣ መንግሥት ከሆነ በኋላም ተግባራዊ ያደረገው መመሪያው፣ ሥልጣን ከያዘበት ጊዜ አንስቶ በሰፊ የሕዝብ ትግል ከሥልጣን እስኪወርድ ድረስ የኢትዮጵያን ሕዝብ ፍዳውን አሳይቶታል፡፡ በሚያሳዝን ሁኔታም በሕዝቡ ትግል ላይ ተንጠልጥሎ፣ አሁን በሥልጣን ላይ ያለው የብልጽግና መንግሥት ወደ ሥልጣን ለመምጣት እንዲያመቸው ያወገዘውን የአክራሪ ብሔርተኝነት መመሪያ ከአመለካከት ጀምሮ እስከ ሕገ-መንግሥቱን ማክበር ድረስ በማስኬድ ሕዝባችንና አገራችንን ከጦርነት ወደ ጦርነት በማስገባት ለዘመናት የኖረውን የአንድነት ቋጠሮ በመበጣጠስ ላይ ይገኛል፡፡

ይህ መንግሥት እየነጣጠለ ለማጥቃት እቅድ አውጥቶ እየተንቀሳቀሰ ስለሆነ ዛሬ በአማራ ሕዝብ ላይ የሚዘንበው ጦርነት ነገ ወደ ሌሎች ክልሎች የሚዛመት በመሆኑ በተናጠል ከመጠቃት በአንድነት ቆመህ ለመብትህ እንድትታገል ኢሕአፓ ወገናዊ ጥሪውን ያቀርባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአሁኑ ሰዓት በአማራ ሕዝብ ላይ የሚደረገው አፈናና ጭፍጨፋ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ጉዳይ መሆኑን በማመን ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች በአንድነት በመቆም ይህን

ስልክ / Phone: +251 911 400 982 ኢሜይል / email: eprp@eprp-ihapa.com

እኩይ ድርጊት በጋራ እንድናወግዘውና የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል አጠናክረን ትግሉን እንድናፋፍም ኢሕአፓ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!

ነሃሴ 15 ቀን 2015 ዓ. ም

ስልክ / Phone: +251 911 400 982ኢሜይል / email: eprp@eprp-ihapa.com